Seattle Public Utilities

# የ 2021-23 መመሪያዎች

# Waste-Free Communities Matching Grant (ከብክለት ነፃ የሆኑ ማህበረሰቦች የማቹንግ ድጎማ)

## ማመልከቻዎች በ ኤፕሪል 16፣ 2021 እስከ 5:00 PM ድረስ መግባት አለባቸው

Seattle Public Utilities (SPU፣ የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች) አሁን በቆሻሻ ላይ ላተኮሩ የማህበረሰብ ፕሮጀክቶች የማቹንግ ድጋፎችን ለመስጠት ማመልከቻዎችን እየተቀበለ ነው፡፡ ቆሻሻን መከላከል ማለት አነስተኛ ቁሳቁሶች መልሰው ጥቅም እንዲሰጡ፣ ማዳበሪያ፣ እና ቆሻሻ መጣያ ውስጥ እንዲገቡ ለማድረግ አነስተኛ ብክነትን መፍጠር ማለት ነው፡፡ ብክነትን በምንከላከልበት ጊዜ፣ አካባቢን እንረዳለን፣ የህብረተሰብ ጤናን እንጠብቃለን፣ ማህበረሰብን እንገነባለን፣ እንዲሁም ገንዘብ እንቆጥባለን፡፡

የድጎማ ፕሮግራም ዓላማዎች፡-

- በቆሻሻ መከላከል ዙሪያ የህብረተሰቡን አመራር እና ፈጠራን ይደግፉ
- ለህብረተሰቡ የቆሻሻ መከላከልያ እድሎችን ተደራሽነት ያሳድጉ
- ሀብቶችን በመጠበቅ/በመቆጠብ እና የግሪን ሃውስ ጋዞችን እና ብክለትን በመቀነስ አካባቢውን ይጠብቁ
- በሲያትል ውስጥ የሚባክኑትን የቁሳቁሶች መጠን ይቀንሱ

የገንዘብ ድጋፍ፡-

- ይህንን የእርዳታ ውደት ለመሸለም አጠቃላይ $200,000 አለ፡፡
- የስጦታ ጥያቄዎች ከ $3,000 እስከ $40,000 ሊደርሱ ይችላሉ፡፡ SPU አነስተኛ ወይም ከፍተኛ መጠኖችን የመሸለም መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
- የስጦታ ሽልማቶች ገንዘብን በማወራረድ/ወጪን በማካካስ መሠረት ይከፈላሉ፡፡
- ፕሮጀክቶች ከኦገስት 2021 በፊት ላይጀምሩ ይችላሉ፡፡ ገንዘብ ከጁን 30፣ 2023 ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል እና ደረሰኝ መግባት አለበት፡፡
- 25% የማች መስፈርት አለ፡፡ ምሳሌ፡- $40,000 የገንዘብ ድጋፍ + $10,000 ማች = $50,000 ጠቅላላ የፕሮጀክት በጀት፡፡

## ስለ ቆሻሻ መከላከል

ሪሳይክል ማድረግ እና ማዳበሪያ መስራት በጣም ጥሩ ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ቆሻሻ አለመፍጠር ግን የበለጠ የተሻለ ነው!

የምንገዛው ወይም የምንጠቀምበት ማንኛውም ነገር የሚጀምረው ምርትን እና ማሸጊያው ለማዘጋጀት ሃብቶችን በመጠቀም፣ በማጓጓዝ፣ በመጠቀም እና በመቀጠል ሪሳይክል በማድረግ፣ ማዳበሪያ በማድረግ ወይም መሬት ላይ በመጣል ነው፡፡ ይህ ሁሉ በምንተነፍሰው አየር፣ በምንጠጣው ውሃ እና ምግብ በምናበቅልበት አፈር ላይ ትልቅ ተጽህኖ አለው፡፡

በሚከተሉት ብክነትን መከላከል እንችላለን፡-

- ያነሰ በመግዛት እና በመጠቀም
- ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆዩ ምርቶችን በመስራት ወይም በመግዛት
- ያገለገለ ነገር በመግዛት
- አነስተኛ ማሸጊያዎችን በመጠቀም
- ለመጠገን እና እንደገና ለመጠቀም በመምረጥ
- ሌሎች እንደገና እንዲጠቀሙባቸው እቃዎችን ማጋራት፣ መለገስ ወይም እንደገና መሸጥ
- በቦታው ላይ የምግብ እና የጓሮ ቆሻሻን በማዘጋጀት እና በመጠቀም

ብክነትን ለመከላከል እርምጃ በመውሰድ፣ እኛ፡-

- ያነሰ በመግዛት እና በመጠቀም ገንዘብ እንቆጥባለን
- ቁሳቁሶችን በመለገስ እና በማካፈል ማህበረሰባችንን እንረዳለን
- የሰውን ጤንነት እና የዱር እንስሳትን የሚጎዳ የአየር እና የውሃ ብክለትን እንቀንሳለን
- እንደ ውሃ፣ ኃይል፣ መሬት እና ነዳጅ ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን እንቆጥባለን
- የአየር ንብረት ለውጥን የሚያስከትሉ የግሪንሃውስ ጋዝ ልቀቶችን እንቀንሳለን

## የፕሮግራም/የፕሮጀክት መስፈርቶች

ፕሮፖሳሎች/የሃሳብ እቅዶች ለማመልከት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፦

1. እንቅስቃሴዎች ብክነትን መከላከል አለባቸው።

   የሚከተሉት ተግባራት ለእርዳታ ገንዘብ ብቁ አይደሉም፦

   - ሪሳይክል ማድረግ
   - ከቦታ ውጭ ማዳበሪያ (ሌላ ቦታ የተዘጋጀ እና ጥቅም ላይ የዋለ)
   - ሪሳይክል ወይም ማዳበሪያ የሚደረጉ ምርቶችን መጠቀም
   - በቆሻሻ መከላከል ላይ ያላተኮሩ የቆሻሻ ማጽዳት ተግባራት
   - የቢስክሌት እና የመኪና ድርሻዎች

2. እንቅስቃሴዎች በ የሲያትል ከተማ ወሰን ውስጥ መከናወን አለባቸው ወይም በሲያትል ውስጥ በቆሻሻ ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ ማሳደር አለባቸው። ፕሮጀክቱ በሲያትል ላይ ያተኮረ ከሆነ፥ አመልካቾች ከሲያትል ውጭ ሊገኙ ይችላሉ።

   የሲያትል ከተማ ወሰን ካርታ ይመልከቱ፦ http://clerk.ci.seattle.wa.us/~public/nmaps/fullcity.htm

3. እንቅስቃሴዎች ከሚከተሉት ምድቦች በአንዱ ውስጥ መግባት አለባቸው፦

**ምድብ 1፦ አዲስ/የተስፋፉ የቆሻሻ መከላከል ተግባራት**

በአዲስ ወይም በተስፋፉ የቆሻሻ መከላከል ስራዎች ላይ ያተኮሩ ሀሳቦች ከሚከተሉት የትኩረት አቅጣጫዎች ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ማካተት አለባቸው፦

| ፈጠራ | የማህበረሰብ ተሳትፎ | የማህበረሰብ ጥቅሞች |
|---|---|---|
| አዳዲስ አቀራረቦችን ይፈትኑ ወይም ያስፋፉ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ያዳብሩ፣ ወይም አዲስ የቆሻሻ መከላከል እድሎችን ወደ ሲያትል ያምጡ። | የቀለም፣ የኢሚግራንት፣ የስደተኞች፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው፣ የአካል ጉዳተኞች፣ አዛውንቶች፣ ወጣት ጎልማሳዎች፣ ወጣቶች፣ ልጆች፣ እና/ወይም አነስተኛ ንግዶች ማህበረሰቦችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ማሳተፍ። | ነፃ ወይም ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸውን ሀብቶች ወይም ቤት ለሌላቸው እና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የማህበረሰብ አባላት የሥራ ሥልጠናን በመስጠት የሲያትል ማህበረሰቦችን መርዳት |
| <u>የቀደምት/ያለፉ ፕሮጀክቶች ምሳሌዎች፦</u><br>• ደንበኞች በተደጋጋሚ የሚጠቀሙትን የምግብ ማያዣ አማራጮችን ለማቅረብ ከምግብ ቤቶች ጋር መተባበር<br>• ለአዳዲስ ግንባታ የተመለሰውን ጣውላ ለመጠቀም የንግድ ስራን ማሳየት | <u>የቀደምት/ያለፉ ፕሮጀክቶች ምሳሌዎች፦</u><br>• በማህበረሰብ ጥገና ኹነቶች ላይ ለመሳተፍ አዛውንቶችን መመልመል<br>• አነስተኛ ንግዶችን ብክነትን በመከላከል ገንዘብ እንዲቆጥቡ መርዳት | <u>የቀደምት/ያለፉ ፕሮጀክቶች ምሳሌዎች፦</u><br>• ኢሚግራንት እና ስደተኛ ሴቶችን ከባከነ ጨርቃጨርቅ የተሠሩ የቤት እቃዎችን እንዲፈጥሩ እናእንዲሸጡ መቅጠር<br>• ከአፓርታማ ተከራዮች ለቀው ሲወጡ የማይበሰብስ ምግብ ሰብስበው ለአከባቢው የምግብ ባንኮች መለገስ |

**ምድብ 2፦ ለቀጣይ ቆሻሻ መከላከል ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች፣ እና አሰራሮች ከ COVID ማገገሚያ ድጋፍ**

ለ 2021-23 የእርዳታ ዑደት ብቻ፣ SPU በ COVID የተጎዱ ቀጣይነት ላላቸው የቆሻሻ መከላከል ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች፣ እና አሰራሮች ገንዘብ ለመስጠት የእርዳታ ፕሮግራሙን እያሰፋ ነው ። ይህ ድጋፍ በቆሻሻ መከላከል ላይ ያተኮሩ የንግድ ተቋማትን እና በ COVID ምክንያት በገንዘብ ችግር ውስጥ ያሉ ድርጅቶችን ለማቆየት የታሰበ ነው።

## ማመልከት ያለበት ማነው

SPU ማመልከቻዎችን ከሚከተሉት ያበረታታል፦

- ከንግዶች
- ለትርፍ ካልተቋቋሙ ድርጅቶች
- ከማህበረሰብ እና ከሰፈር ቡድኖች
- ትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆች፣ እና ዩኒቨርስቲዎች
- ተቋማት (እንደ ጤና አጠባበቅ ወይም መኖሪያ ቤት ያሉ)
- በእምነት ላይ የተመሰረቱ ድርጅቶች
- የወጣቶች እና የልጆች ፕሮግራሞች

አመልካቾች ከአንድ በላይ ማመልከቻዎችን ማቅረብ ይችላሉ ነገር ግን አንድ የድጎማ ሽልማት ብቻ ለመቀበል ብቁ ናቸው።

ሁሉም አመልካቾች የገንዘብ ድጎማዎችን ለመቀበል፣ ወይም አስፈላጊ በሆኑ ፈቃዶች በፊስካል/የገንዘብ አያያዝ ወኪል በኩል ለመስራት የዋሺንግተን ግዛት እና የሲያትል ከተማ የንግድ ፈቃዶች ሊኖራቸው ይገባል። የፊስካል/የገንዘብ አያያዝ ወኪል ለፕሮጀክትዎ የእርዳታ ገንዘብን ለመቀበል እና ለማስተዳደር ኃላፊነቱን ይወስዳል።

**የሲያትል ከተማ የንግድ ስራ ፈቃድ መረጃ፡-** https://www.seattle.gov/licenses/get-a-business-license/cost-of-a-business-license።
**የዋሺንግተን ግዛት የንግድ ስራ ፈቃድ መረጃ፡-** http://bls.dor.wa.gov/faqlicense.aspx

## እንደገና ማመልከት

አመልካቾች ለእያንዳንዱ የገንዘብ ድጋፍ ዑደት እንደገና ማመልከት ይችላሉ፡-

- የገንዘብ ድጋፍ ባልተሰጠው ፕሮጀክት እንደገና ማመልከት ለሚቀጥለው የገንዘብ ድጋፍ ዑደት እንዴት ማመልከቻዎን ማሻሻል እንደሚችሉ ለማወቅ እንዲያነጋግሩን እንመክራለን።
- በአዲስ የፕሮጀክት ሀሳብ ማመልከት።
- ቀደም ሲል በገንዘብ የተደገፈ ፕሮጀክት ለማስፋት ወይም ቀጣዩን ምዕራፍ ለመተግበር ማመልከት። ማመልከቻው የተሻሻለ የቆሻሻ መከላከልን ማሳየት አለበት።

## የገንዘብ ድጋፍ እና የማች መስፈርቶች

**የገንዘብ ድጋፍ፡-**

- ይህንን የእርዳታ ዑደት ለመሸለም አጠቃላይ $200,000 አለ።
- የስጦታ ጥያቄዎች ከ $3,000 እስከ $40,000 ሊደርሱ ይችላሉ። SPU አነስተኛ ወይም ከፍተኛ መጠኖችን የመሸለም መብቱ የተጠበቀ ነው።
- በእርዳታ ስምምነቱ ውስጥ የተለዩ ወሳኝ ድርጊቶችን በማጠናቀቅ መሰረት የእርዳታ ገንዘብ ተመላሽ በሆነው መሰረት ይከፈላል።
- የእርዳታ ገንዘቦች ከጁን 30፣ 2023 ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል እና ደረሰኝ መግባት አለበት።

**የማች መስፈርቶች**

- ማቹ ከእርዳታ ጥያቄው ቢያንስ 25% መሆን አለበት (ከተማው ለሚሰጠው እያንዳንዱ ዶላር 25 ሳንቲም ዋጋ)። ምሳሌ፡- $40,000 የገንዘብ ድጋፍ ጥያቄ + $10,000 ማች = $50,000 ጠቅላላ የፕሮጀክት በጀት።
- የማች መዋጮ በዓይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ ሊሆን ይችላል።
- እንደ ከተማ ሰራተኛ ሰዓት፣ የከተማ መገልገያዎችን አጠቃቀም፣ እና/ ወይም ሌላ የከተማ ገንዘብን የመሳሰሉ የሲያትል ከተማ ሀብቶች እንደ ማች አካል አይቆጠሩም።

**የወጪ ምድቦች፡-**

የሚከተሉት በፕሮጀክትዎ የእርዳታ ጥያቄ እና በማች ውስጥ ሊያካትቷቸው የሚችሏቸው ወጪዎች ምሳሌዎች ናቸው፡-

- የሰራተኛ ሰዓት (ኦቨርሄድን ሊያካትት ይችላል)
- ለተሳትፎ አበሎች እና ሌሎች ማበረታቻዎች
- ያልተከፈለ የበጎ ፈቃደኝነት ጊዜ (በሰዓት $33.02 በሆነ በዋሽንግተን ግዛት የበጎ ፈቃደኝነት ጊዜ ገለልተኛ ዘርፍ ዋጋ ላይ በመመስረት)
- አቅርቦቶች፣ ቁሳቁሶች፣ እና መሳሪያዎች
- እንደ ትርጉም፣ ህትመት፣ እና ዲዛይን ያሉ አገልግሎቶች
- የቦታ ኪራዮች
- የአልኮል መጠጦችን ሳይጨምር፣ ለፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች ምግብ እና መጠጥ
- ማይሌጅ እና የመኪና ማቆሚያ (አሁን ባለው የፌደራል ማይል ተመን ዋጋ)
- የፊስካል/የገንዘብ አያያዝ ወኪል ክፍያዎች (የእርዳታን ጥያቄ እስከ 10%)

## ውል እና ክፍያ

**ውል፡-**

- የሽልማት ተቀባዮች የራሳቸውን የእርዳታ ገንዘብ ማስተዳደር ወይም የፊስካል/የገንዘብ አያያዝ ወኪልን መጠቀም ይችላሉ። የሽልማት ተቀባዮች የፊስካል/የገንዘብ አያያዝ ወኪልን ላለመጠቀም የሚመረጡ የራሳቸውን የግብር መታወቂያ ቁጥር ማቅረብ እና የ Internal Revenue Service (የውስጥ ገቢ አገልግሎት) ደንቦችን ማክበር አለባቸው።
- እያንዳንዱ የሽልማት ተቀባይ ወይም የፊስካል/የገንዘብ አያያዝ ወኪላቸው የእርዳታ ገንዘብ ለመቀበል ከ SPU ጋር ስምምነት መፈረም አለባቸው። ስምምነቱ የእርዳታውን ተጨማሪ ውሎች እና ሁኔታዎችን ያጠቃልላል።
- እርዳታው ከከተማው ጋር ስምምነት ከተፈረመ በኋላ ለሚከናወኑ የፕሮጀክት ተግባራት ብቻ ይከፍላል።

**የፊስካል/የገንዘብ አያያዝ ወኪሎች፡-**

- አመልካቾች ለፕሮጀክቱ የእርዳታ ገንዘብን ለመቀበል እና ለማስተዳደር ኃላፊነቱን ከሚወስድ የፊስካል/የገንዘብ አያያዝ ወኪል ጋር ለመስራት ይመርጡ ይሆናል።
- አመልካቾች የራሳቸውን የፊስካል/የገንዘብ አያያዝ ወኪል በመለየት እና የፊስካል ወኪሉ የወቅቱ የዋሽንግተን ግዛት እና የሲያትል የንግድ ፍቃዶች እንዳላቸው የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው።
- የፊስካል/የገንዘብ አያያዝ ወኪል ክፍያዎች የእርዳታውን መጠን እስከ 10% ያህል ሊያከፍሉ ይችላሉ። አመልካቾች ይህንን ክፍያ በእርዳታ ጥያቄው ውስጥ ሊያካትቱ ወይም በማች መዋጮ ላይ ማመልከት ይችላሉ።

**የመድን መስፈርቶች፡-**

የእርዳታ ተቀባዮች ከእርዳታ ፕሮጀክቱ ስፋትና ተፈጥሮ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ስራ ለሚያከናውኑ የንግድ ሥራዎች የዋሽንግተን ግዛት ሕግ ከሚያስፈልገው ያላነሰ የመድን ሽፋን ደረጃቸውን መጠበቅ አለባቸው። በዋሽንግተን ግዛት ሕግ የሚጠየቅ ከሆነ የሰራተኞች የካሳ መድን እንዲሁ ሊቆይ ይገባል።

**ክፍያ፡-**

በእርዳታ ስምምነቱ ውስጥ ባለው የተለዩ ወሳኝ ድርጊቶችን በማጠናቀቅ ስምምነት መሰረት የስጦታው ተቀባዮች ደረሰኞችን ያስገባሉ። SPU እያንዳንዱ የክፍያ መጠየቂያ ደረሰኝ ከደረሰ ከ 30 ቀናት በኋላ ተመላሽ ገንዘብ ቼኮችን በፖስታ ይልካል። የክፍያ መጠየቂያዎች ያልተጠናቀቁ ወይም አስፈላጊ ሪፖርቶች እና ሰነዶች ከሌሉ ክፍያው ይዘገያል።

**ሪፖርት ማድረግ፡-**

- የሽልማት ተቀባዮች ከእያንዳንዱ የሂሳብ መጠየቂያ ደረሰኝ ጋር የሂደቱን ሪፖርት እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ።
- የሽልማት ተቀባዮች የመጨረሻውን የገንዘብ ድጎማ ክፍያ ከመቀበላቸው በፊት የመጨረሻውን የፕሮጀክት ውጤቶች እና የተማሩትን ትምህርቶች የሚያጋሩ ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው።

## የማመልከቻ ግምገማ

**የግምገማ ኮሚቴ፡-**

የእርዳታ ግምገማ ኮሚቴው ከተለያዩ መነሻ እና የሙያ ዘርፎች የተውጣጡ የማህበረሰብ አባላት እና የሲያትል ከተማ ሰራተኞች ናቸው። SPU አመራር የመጨረሻ የገንዘብ ድጋፍ ውሳኔ ሲያደርግ የግምገማ ኮሚቴ ምክሮችን ከግምት ውስጥ ያስገባል።

**የግምገማ መስፈርት/መመዘኛ፡-**

የእርዳታ ግምገማ ኮሚቴው ከዚህ በታች በተገለፁት መመዘኛዎች መሠረት ለፕሮጀክቶች ቅድሚያ ይሰጣል። SPU እንዲሁም በጂኦግራፊያዊ አካባቢ፣ ተጽዕኖ በደረሰባቸው ማህበረሰቦች እና የፕሮጀክቶች ዓይነቶች ብዝሃነትን ይመለከታል። SPU የመጨረሻውን የገንዘብ ውሳኔ ከማድረጉ በፊት አመልካቾችን በክትትል ጥያቄዎች አማካይነት ሊያነጋግራቸው ይችላል።

1. **ቆሻሻን የመከላከል ውጤቶች፦** የፕሮግራም/የፕሮጀክት ብክነትን የመከላከል አቅም።

    - እንቅስቃሴ ለ SPU ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጡ ቁሳቁሶች ብክነትን ይከላከላል (ምሳሌዎች፦ ምግብ፣ ጨርቃ ጨርቆች፣ አንድ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉ ፕላስቲኮች እና ሌሎች አንድ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉ የምግብ አገልግሎት ቁሳቁሶች፣ የግንባታ ቁሳቁሶች፣ ዳይፐሮች)
    - የእንቅስቃሴው ያሉት ብክነትን የመከላከል አቅም እና ተዛማጅ የአካባቢ ተጽዕኖዎች
    - እንቅስቃሴው ውጤታማ በሆኑ መንገዶች የመድረስ አቅም ያለው የሰዎች ብዛት
    - እንቅስቃሴ የቆሻሻ መከላከል ውጤቶችን ለመለካት ይችላል
    - እርዳታው ከተጠናቀቀ በኋላ የቆሻሻ መከላከል ተጽዕኖዎች ይቀጥላሉ

2. **አቅም፦** አቅም ላይ በመመርኮዝ የፕሮግራም/የፕሮጀክት ስኬታማ መሆን።

    - ፕሮግራሙ/ፕሮጀክቱ ስኬታማ ለመሆን በቂ ሰራተኞች፣ አጋሮች፣ በጎ ፈቃደኛ ሰራተኞች፣ እና የገንዘብ ሀብቶች አሉት
    - ሰራተኞች፣ በጎ ፈቃደኞች፣ እና አጋሮች አስፈላጊ እውቀት፣ ክህሎቶች፣ ልምዶች እና ግንኙነቶች አሏቸው
    - አስፈላጊ ከሆነ አጋርነቶች ቀድመው የተረጋገጡ ናቸው

3. **በጀት፦** በታቀደው በጀት ላይ በመመርኮዝ የፕሮግራም/የፕሮጀክት ስኬታማ መሆን።

    - በጀት ከቀረበው ሀሳብ ጋር ይጣጣማል
    - የበጀት ግምቶች ትክክል ናቸው
    - ሁሉም ወጭዎች ለእርዳታው አግባብ ናቸው
    - ለተጠበቀው ውጤት የተጠየቀው መጠን ተመጣጣኝ ነው

4. ***ምድብ 1 ብቻ፦ በአዲስ ወይም የተስፋፉ የቆሻሻ መከላከል ስራዎች*** - *ፕሮጀክቶች ከሚከተሉት የትኩረት አቅጣጫዎች ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ማካተት አለባቸው*

    ***ፈጠራ፦*** የአንድ ፕሮጀክት አዲስ አቀራረቦችን ወይም ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም።

    - ፕሮጀክቱ ለሲያትል አካባቢ ፈጠራን ያማከለ ነው
    - ፕሮጀክቱ በሲያትል ማህበረሰብ ውስጥ በሌሎች የመባዛት አቅም አለው
    - ፕሮጀክቱ በሲያትል ውስጥ ከፍተኛ ተጽዕኖ ለማሳደር የማደግ አቅም አለው
    - ፕሮጀክቱ ዘዴዎችን እና ውጤቶችን ከህብረተሰቡ ጋር ይጋራል

    **የማህበረሰብ ተሳትፎ፦** በቆሻሻ መከላከል ዙሪያ ማህበረሰቦችን በብቃት ለማሳተፍ ያለ የፕሮጀክት አቅም።

    - ፕሮጀክቲ በ SPU ከፍተኛ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ማህበረሰቦችን (የቀለም፣ የኢሚግራንት፣ የስደተኞች፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው፣ የአካል ጉዳተኞች፣ አዛውንቶች፣ ወጣት ጎልማሳዎች፣ ወጣቶች፣ ልጆች፣ እና/ወይም አነስተኛ ንግዶችን) ያሳትፋል።
    - ፕሮጀክቱ ለተመልካች(ቶች) ውጤታማ የተሳትፎ ስልቶችን ይጠቀማል
    - ፕሮጀክቱ በፕሮጀክት እቅድ እና ትግበራ ላይ ተጽዕኖ ያደረባቸውን ማህበረሰቦችን ያካትታል

    **የማህበረሰብ ጥቅሞች፦** የፕሮጀክቱ ለማህበረሰቡ ጥቅማጥቅሞችን የማቅረብ አቅም።

    - ፕሮጀክቱ በጣም ለተቸገሩ ሰዎች (እንደ ቤት አልባ ወይም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ማህበረሰቦችን) ይጠቅማል
    - የተለዩ ጥቅሞች ለተጎዱት ማህበረሰቦች (እንደነፃ ወይም ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸውን ሀብቶች ወይም የሥራ ሥልጠና መስጠት) ዋጋ ይኖራቸዋል

5. **ምድብ 2 ብቻ፦ ለቀጣይ ቆሻሻ መከላከል ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች፣ እና አሰራሮች ከ COVID ማገገሚያ ድጋፍ**

    - በ COVID ወቅት ቀጣይነት ያለው የቆሻሻ መከላከል ሥራዎች ፍላጎቶች ጨምረዋል፣ እንደ ምግብ መስጠት፣ ወይም በመካሄድ ላይ ያሉ የቆሻሻ መከላከል ሥራዎች COVID ባመጣው የገንዘብ ችግር ምክንያት የመቆም፣ የመቀነስ ወይም የመሰረዝ አደጋ ተጋርጦባቸዋል
    - የገንዘብ ድጋፍ መስጠቱ አመልካቹ የቆሻሻ መከላከል ስራዎችን እንዲቀጥል በመርዳት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል
    - ህብረተሰቡ እየተከናወነ ባለው የቆሻሻ መከላከል ስራ መቀጠል ተጠቃሚ ይሆናል

## የማመልከቻ ሂደት

***መርሃ ግብር፡-***

| | |
|---|---|
| **የማመልከቻ ማብቂያ** | ኤፕሪል 16፣ 2021 |
| **የውሳኔዎች ማስታወቂያ** | በጁን አጋማሽ |
| **ስምምነቶች በ ከተማ የተፈረሙ (ፕሮጀክቶች ሊጀምሩ ይችላሉ)** | ኦገስት 2021 |
| **ስራ ተጠናቅቋል እና መጠየቂያ ደረሰኝ ገብቷል** | በጁን 30፣ 2023 |

***የማመልከቻ ደረጃዎች፡-***

**ደረጃ 1፡-** ማመልከቻዎን ከማጠናቀቅዎ በፊት መመሪያዎቹን ያንብቡ እና የእርዳታ ትእዛዞች ቪዲዮን ይመልከቱ።

**ደረጃ 2፡-** ፕሮጀክትዎን ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥ እና የፕሮጀክት ምክሮችን ለማግኘት ያግኙን።

**ደረጃ 3፡-** የህትመት ወይም ቪዲዮ ማመልከቻን ያጠናቅቁ (ሁለቱንም አያድርጉ)።

- የህትመት ማመልከቻዎች ከ 7 ገጾች ያልበለጡ መሆን አለባቸው።
- የቪዲዮ ማመልከቻዎች ከ 15 ደቂቃዎች ያልበለጡ መሆን አለባቸው።
- ማመልከቻዎች በሚመርጡት ቋንቋ ሊቀርቡ ይችላሉ። SPU ትርጉምን ያቀርባል።

**ደረጃ 4፡-** የበጀት ቅጹን ያጠናቅቁ።

**ደረጃ 5፡-** ማመልከቻዎን እና ደጋፊ ሰነዶችዎን በ ኤፕሪል 16፣ 2021 እስከ 5:00 PM ድረስ ያስገቡ። በ 2 የስራ ቀናት ውስጥ የደርሶናል ኢ-ሜይል ማረጋገጫ ካልደረሰዎት በ (206) 233-2534 ይደውሉ

## ያግኙን

በእንግሊዝኛ ወይም ከዚህ በታች ባልተዘረዘሩት ቋንቋዎች እገዛ ለማግኘት በ wastefreegrants@seattle.gov ወይም (206) 233-2534 ን ያነጋግሩ።

በሚቀጥሉት ቋንቋዎች እገዛ ለማግኘት አጋራችንን፣ Environmental Coalition of South Seattle (ECOSS፣ የደቡብ ሲያትል አካባቢያዊ ጥምረት) በ dhan@ecoss.orgወይም በ (206) 767-0432 ያነጋግሩ። ለእርዳታ አመልካቾች በቋንቋ የፕሮጀክት ምክር ለመስጠት SPU ለ ECOSS የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል።

- አማርኛ
- ካንቲኒዝ
- ኮሪያኛ
- ማንዳሪን
- ሶማሊኛ
- ስፓኒሽ
- ትግርኛ
- ቪዬትናምኛ